# የስዊድንያኑ ጋዜጠኞች ቅጣት ‹ጫጫታ› መንስዔዎች

ቶሎሳ Utolosa@yahoo.com

ምን ላይ ተጽፎ እንዳነበብኩት ለጊዜው አላስታውስም - ብቻ ከንዋኔው ከብዙ ዓመታት በፊት የተደረገ ነው፡፡ የድርጊቱ አፅመ - ታሪክም በአዕምሮዬ ማስታወሻ መዝገብ ላይ እንዲህ ተከትቦ ቀርቷል፡፡… ‹በአንዲት ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ይጠራራሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ 'በሀገራችን ህግ ውስጥ ሞት ቅጣት መኖር የለበትም' የሚል ነው፡፡ እናም እነዚህ በቁጥራቸው በርከት ያሉ የዚያች ሀገር ዜጎች፣ የሞት ቅጣትን የሚያወግዙ መፈክሮችን አንግበው አደባባዩን አጥለቀለቁት፡፡ 'በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ፣ ህይወቱ ማብቃት ያለበት በፈጣሪው እጅ እንጂ፤ በህግ በተደነገገ ቅጣት መሆን የለበትም' ሲሉም ለመንግስታቸው አቤቱታቸውን አሰሙ፡፡…

… ይሁንና መፈክራቸውን እያስተጋቡ ሳለ፤ ከእነርሱ ትይዩ በሆነ ቦታ ላይ አንድ የተለየ መፈክር የያዘን ግለሰብ ይመለከታሉ፡፡ መፈክሩም እንዲህ ይላል - 'በሀገራችን ህግ ውስጥ የሞት ቅጣት መኖር አለበት፡፡' እናም የሞት ቅጣትን የሚቃወሙት ሰዎች ግር ብለው ወደ ግለሰቡ በመጠጋት በጥያቄ ያጣድፉት ያዙ፡፡ ብቸኛው የሞት ቅጣትን የሚደግፈው ሰው 'የቅጣቱ መኖር ለሌች ወንጀለኞች መቀጣጫ ይሆናል' የሚል አቋሙን በማጠናከር ምላሽ ይሰጥ ገባ፡፡ ሰዎቹም ግለሰቡ የእነርሱን አቋም እንዲይዝ ቢሞክሩም፤ ሰውዬው ሊስማማ አልቻለም፡፡ በዚህ የተናደዱት 'የሞት ቅጣት አያስፈልገንም' ባዩች፤ ግለሰቡን በያዙት መፈክርና በድንጋይ ይቀጠቅጡታል፤ ሰውዬውም ይሞታል፡፡ በዚህ ድርጊታቸውም መኖር የለበትም ያሉትን የሞት ቅጣት ራሳቸው ገቢራዊ በማድረግ ያቀረቡትን ጥያቄ በአደባባይ ሽረውታል፡፡›…

ይህ እውነተኛ ታሪክ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር፤ አንድ ድርጊት ራሳችን ስንከውነው 'ትክክል'፣ ሌሎች ሲፈጽሙት ደግሞ 'የተሳሳተ ነው' የሚል እሳቤ፤ ስሞታ፣ ውግዘትና ጩኸት ተገቢ አለመሆኑን ነው፡፡ ከላይ በጠቀስኩት ታሪክ ውስጥ የሞት

ቅጣትን የሚቃወሙት ሰዎች ራሳቸው ግለሰቡን ሲገድሉ ‘አግባብነት ያለው’፣ መንግስት ደግሞ የሀገሪቱን ሠላምና መረጋጋት ለማስከበር በወንጀለኞች ላይ በህግ አግባብ የሞት ቅጣት እንዲፈፀም የህግ ማዕቀፍ ሲያበጅ ‘አግባብነት የጎደለው’ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህም ነው ዕውቁ የዓለማችን ፈላስፋ ኢማኑኤል ካንት “በራስህ ላይ እንዲፈጸም የማትፈልገው ነገር በሌሎች ላይ አታድርግ ወይም ራስህ እንዲሆንልህ የምትፈልገውን ነገር ለሌሎችም አድርግ” ያለው፡፡

መቼም ውድ አንባቢዎቼ ቀደም ሲል የጠቀስኩትን ታሪክ በትውስታነት ያነሳሁት ስለሞት ቅጣት አስፈላጊነትና አላስፈላጊነት ላውጋችሁ ፈልጌ እንዳልሆነ እንደምትገነዘቡት እርግጠኛ ነኝ፡፡ አዎ! የጽሑፌ ማጠንጠኛ ሰሞኑን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወንጀል ችሎት በሽብርተኝነት ተጠርጥረው ክስ የተመሰረተባቸውን ሁለት ሰዊድናዊያን ጋዜጠኞች ላይ ያሳለፈውን የቅጣት ውሳኔ ተከትሎ፣ እነርሱ ሲያደርጉት ትክክል የሚመስላቸው እና ሌሎች ሀገሮች ሲፈጽሙት ከተለያዩ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጋር በማቆራኘት “ትክክል አይደለም” ባይ ነጮች ያኾጎደጎዱት የወቀሳና የውግዘት ጋጋታ አስገራሚነት ነው፡፡

እርግጥ በአንዲት ሉዓላዊት ሀገር የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ በመግባት “በነጮቹ ጋዜጠኞች” ላይ ነጻና ገለልተኛው ፍርድ ቤት ያስተላለፈውን ውሳኔ፣ የኢትዮጵያ መንግስት እንዲያስቀለብስ የጠየቁ እንዲሁም የተለመዱትን ወቀሳና ውግዘት ያዘነቡ ኃይሎች በርካታ ናቸው፡፡ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፣ ራሱን ‘የጋዜጠኞች መብት ተከላካይ’ እያለ የሚጠራው ሲ.ፒ.ጄ የተሰኘ አክራሪ ድርጅት፣ የስዊዲን መንግስት፣ የአውሮፓ ህብረት የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን፣ ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ቡድን፣ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል፣ ለተከሳሾቹ ከለላ ሰጥቶ ወደ ሀገር ውስጥ ሊያስገባቸው የሞከረው አሸባሪው ኦብነግ ወዘተ. በየፊናቸው ያላወጡት የመግለጫ ጋጋታ የለም፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ‘የስሞታውና የወቀሳው ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት ነጮች ያሰሙት አንድ ዓይነት ጩኸትና ጫጫታ፣ ሁለቱ ፈረንጆች ወንጀለኛ አለመሆናቸውን ስለማያውቁ ነውን?’ የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እንደሚታወቀው ሁለቱ ተከሳሾች ሆን ብለው፣ አስበውና አቅደው በጋዜጠኝነት ሽፋን ከስዊዲን ወደ ለንደን፣ ከለንደን ወደ ኬንያ፣ ከኬንያ ወደ ሶማሊያ፣ ከሶማሊያ ወደ ኦጋዴን በመግባት እንዲሁም

የኢትዮጵያ መንግስት በአሸባሪነት በሰየመው የኦብነግ ታጣቂዎች በመታጀብ በህገ - ወጥ መንገድ ወደ ሀገራችን ገብተዋል፡፡

በዚህም ለህዝብ ደህንነት አስጊ የሆነ ተግባር ለመፈጸም በማሴር የሀገሪቱን የፖለቲካ ሉዓላዊነት በመጣስ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ፍርድ ቤቱ በማረጋገጡ በህጉ መሰረት በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የወንጀለኞቹ ጠበቃ ደንበኞቻቸው ከዚህ በፊት ተከሰው የማያውቁ፣ መልካም ፀባይ ያላቸውና ቤተሰቦቻቸውን የሚረዱ መሆናቸውን የሚገልፅ የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ማቅረባቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ይህም ወንጀለኞቹ በሀገሪቱ ህጎች መሰረት ጥፋተኛ በመሆናቸው ባልተራዘመ ጊዜ ውስጥ ፍትህ ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ እውነታ መሆኑ አስረጅ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

ከዚህ ተጨባጭ ሃቅ በመነሳት “ሁለቱ ጋዜጠኞች” የፈጸሙት ተግባር ወንጀል መሆኑን የመግለጫ ጋጋታው ባለቤቶች ያጡታል ብዬ አልገምትም፡፡ በእኔ እምነት፤ የጩኸቱና የጫጫታው መንስኤ ‘እንዴት ነጮች በጥቁሮች ፍርድ ቤት ውስጥ ይዳኛሉ?!’ ከሚል የዘረኝነት አስተሳሰብ እንዲሁም ነጮቹ እነርሱ የሚያደርጉትን ነገር፣ ሌላው ከሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲተገብረው ‘ለምን?’ እያሉ የሚያራምዱትን ርዕዮተ - ዓለም በዚያ ሀገር ላይ በሰበብ አስባቡ ለመጫን የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው፡፡

ይህን የነጮች አተያይ አንባቢዎቼ በውሉ እንዲገነዘቡት ሁለቱንም መንስዔዎች ቀደም ሲል ከተፈጸሙ ነባራዊ ክስተቶች ጋር በማቆራኘት ተራ በተራ እንዲህ እንመለከታቸዋለን፡፡ ... እስቲ በቅድሚያ ወንጀለኞቹ ቀለማቸው ነጭ ስለ ሆነ ብቻ ወደተሰነዘሩት ወቀሳዎችና ስሞታዎች እናምራ፡፡...

እንደ እውነቱ ከሆነ የአንድን ሀገር ሉዓላዊ ግዛት በህገ - ወጥ መንገድ በመጣስ ሀገራችን አሸባሪ ብላ ከሰየመችው ኦብነግ ጋር መሣሪያ ይዘው የተማረኩት የ”ሁለቱ ጋዜጠኞች” ድርጊት ወንጀል መሆኑን የወቀሳ “ጫጫታ” በማሰማት ላይ የሚገኙት ነጮች ይስቱታል ብዬ አልገምትም፡፡ ፈረንጆቹ ይህንን ሃቅ እስካልሳቱ ድረስ ደግሞ፤ በሀገራችን የህፍትህ ሥርዓት ውስጥ እጃቸውን በማስገባት የህግ የበላይነትን “በጫጫታ” ለማስቀልበስ የመፈለጋቸው ምስጢር ከማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ዓላማቸው ያለ አንዳች አሳማኝ አምክንዮ ለነጮች ጥብቅና የመቆም አካሄድ በመሆኑ ነው፡፡

አንድ ጥቁር ቀለም ያለው ጋዜጠኛ በተመሳሳይ መልኩ የነጮችን የግዛት ሉዓላዊነትን ከአሸባሪዎች ጋር በመተባበር ጥሶ ቢገኝ፤ በሀገራቸው ህግ መሰረት ተገቢውን ቅጣት ውሳኔ እንደሚያገኝ እየታወቀ፣ የኢትዮeያ ፍርድ ቤት በሁለቱ ስዊድናዊያን ላይ የቅጣት ዉሳኔ ማስተላለፉ ለምን የ"ጫጫታ" አቧራ እንዳስነሳ ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም ጋዜጠኞቹ ነጮች በመሆናቸው 'ለምን በጥቁሮች ፍርድ ቤት ይቆማሉ?' ከሚል ጊዜው ያለፈበት አስገራሚ አስተሳሰብ የመነጨ ነው፡፡

በእኔ እምነት እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ከአፍሪካ ልሳነ- ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከአፓርታይድ ሥርዓት ጋር ተቀብሯል፡፡ እናም ዛሬ ይህን መሰሉን ፀያፍ አስተሳሰብ የሚሰማ አፍሪካዊ መሪም ይሁን ህዝብ አለ ብሎ ማሰብ ነባራዊ ዕውነታንና ታሪክን አለማወቅ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት አፍሪካዊያን ለነጭም ሆነ ለጥቁር ያለ አድልኦ እኩል የሚያገለግል የህግ ማዕቀፍ ቀርጸው ገቢራዊ እያደረጉ በመሆናቸው ነው፡፡ በተለይም ሀገራችን ማንኛውንም ወንጀለኛ (ነጭም ሆነ ጥቁር) በእኩል ዓይን የምትመለከት እንዲሁም የህግ አግባብን ተከትላ ባለመብት ለሆነው ፍርድ ቤት የማቅረብ ታሪክ ያላት መሆኗን ነጮቹ ቢገነዘቡት መልካም ይመስለኛል፡፡

እንኳንስ በአሁኑ ወቅት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ህዝቡ ሉዓላዊ ግዛቱን እንዲያስከብርላት ከአደራ ጋር የመረጠው የኢፌዴሪ መንግስት ቀርቶ፤ ቀደምት አምባገነናዊ መንግስታትም ቢሆኑ ከሀገር ሉዓላዊነት ወንጀል ጋር በተያያዘ ተደራድረው አያውቁም፡፡ ማንኛውም የኢትዮጵያ መንግስት ነጭም ይሁን ጥቁር በግዛት መጣስ ወንጀል ተግባር ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ግለሰቦችን ያልቀጡበትን ወቅት ማስታወስ አስቸጋሪ ነው፡፡

ይህ ሁኔታም ኢትዮጵያዊያን በሉዓላዊ ግዛታቸው ዙሪያ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡና የህልውናቸውም አካል አድረገውት ይንቀሳቀሱ እንደነበር አስረጅ ነው፡፡ እርግጥም እነርሱ ይህን በማድረጋቸው ነው – ሀገራችን በነጮች ቅኝ ግዛት እጅ ሳትወድቅ ነጻነቷን አስጠብቃ እስከ ዛሬ ድረስ ልትዘልቅ የቻለችው፡፡

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግስትና ህዝቡም ሉዓላዊ ግዛትን ከማስጠበቅ አኳያ ከዚህ የተለየ እሳቤን ይከተላሉ ማለት አይቻልም፡፡ የፌዴራሉ መንግስት ካለፉት ሥርዓቶች ጋር የሚለያይባቸው እጅግ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም፤ ከሰሞነኛው

“ጩኸት” አንጻር የተጀመረው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እንዳይስተጓጎል፣ የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት የማስጠበቅ ህዝባዊ ግዴታ ያለበት እንዲሁም የሚያከናውናቸው ተግባራት ከዴሞክራሲያዊ አሰራሮች የተመሰረቱ መሆናቸውን ብቻ ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ሁለቱ ስዊድናዊያን የሀገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት የሚጻረሩ ተግባራትን ሲፈጽሙ በሶማሌ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይል ከአሸባሪው ኦብነግ ታጣቂዎች ጋር መማረካቸው ወንጀለኛ እንደሚያደርጋቸው ከነጭም ይሁን ከጥቁር ሰው አዕምሮ የሚሰወር ጉዳይ አይደለም፡፡

ዴሞክራሲያዊው መንግስትም የሀገሪቱን የህግ የበላይነት ማረጋገጥ ስላለበት መብታቸው ሳይጓደል አግባብ ባለው ሁኔታ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ በየትኛውም ዴመክራሲያዊ ሀገር የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ምናልባት ነጮቹ አንድን ወንጀለኛ ቀለሙ ነጭ ወይም ጥቁር በመሆኑ የሚሰጡት ቅጣት ይለያይ ካልሆነ በስተቀር፤ የህግ የበላይነት በማንኛውም ሰው ላይ እንጂ፤ የቀለምን መንጣት ወይም መጥቆር ከግምት ውስጥ አስገብቶ የሚከናወን ተግባር አይደለም፡፡ ይህን ሃቅ ለዴሞክራሲ ልዕልና ቆመናል የሚሉትና ዛሬ ‘ጥቁሮች እንዴት ነጮችን ይቀጣሉ?!’ በማለት ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች እንዲቀለበሱ በመግለፃጫ ጋጋታ የሚጠይቁት ነጮች ያጡታል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡

እርግጥም የነጮቹ ፍራቻ ግልጽ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም ‘ኢትዮጵያ የጀመረችውን ወንጀለኛ የሆነን ጥቁርም ሆነ ነጭ ፍርድ ቤት የማቆም አካሄድን ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ይከተሉታል’ የሚል ስጋት ነው፡፡ ምንም እንኳን ‘ስጋታቸው ነጮች በጥቁሮች የፍርድ ሂደት መዳኘት አግባብ አይደለም’ የሚል ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ መንግስት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለእንዲህ ዓይነቱ ጎታች እና ኢ - ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ቦታ ይሰጣል ብዬ አላስብም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊያን በህገ - መንግስታቸው ላይ “ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው” የሚል ገዥ አንቀፅ ከትበው እየሰሩበት በመሆኑ፤ ስለ ነጭም ይሁን ስለ ጥቁር የበላይነት ለመስማት እንደማይፈልጉ፣ ሀገራችንንና ህዝቦቿን የማያውቋት እነዚህ ኃይሎች ሊገነዘቡት ይገባል ባይ ነኝ፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ሁለቱ ስዊድናዊያን የተቀጡት ራሳቸውን ከአሸባሪዎች ጋር በማጣመር በህገ - ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ በመግባታቸው እንጂ፤ ፕሬስን በተመለከተ ከዘገባ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሰዎቹ በህገ - ወጥነታቸው እንጂ በጻፉት ጉዳይ ውሳኔው አልተላለፈባቸውም፡፡ ነገር ግን "የነጮችን የበላይነት" ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ኃይሎች ሃቁን እያወቁ፣ ሁኔታውን በማጣመም ነገሩን ከሚዲያ ስራ ጋር ለማያያዝ የመሞከራቸው ምስጢር፤ በገሃድ ለመናገር የማይፈልጉትን የጥቁርና የነጭ ንጽጽርን ለመሸፈን ከመሆን የዘለለ ትርጉም የሚሰጠው ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

እስቲ እዚህ ላይ ለአብነት ያህል በሁለት ወገኖች የወጡ ስሞታዎችን በደምሳሳው እንመልከት፡፡…አንድን ነገር ሳያረጋግጥ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሀገራችንን አስመልክቶ ወረቀት ላይ ቀለም መለቅለቅ የማይሰለቸውና ራሱን ለይስሙላ 'የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ነኝ' እያለ የሚጠራው እንዲሁም የቀለም አብዮት አቀጣጣይ የሆነውን የ"ሲ.ፒ.ጄ" ን መግለጫ ተብዬ መመልከት ይቻላል፡፡ የሀገራችን ሚዲያ ነጻና ኃላፊነት የሚሰማው ሆኖ እንዲሰራ ዕገዛ የሚያደርገውን፣ ነገር ግን ለጎዳና ላይ ነውጥ አራማጆች ምቹ ያለሆነውን የፀረ - ሽብርተኝነት ህግን ለማውገዝ በመግለጫ አስታክኮ "… የኢትዮጵያ መንግስት የፀረ - ሽብርተኝነት ህጉን በመጠቀም ነጻ ሚዲያን ቀጥቷል" በማለት ብሶቱን ለማስተጋባት ሞክሯል፡፡

መቼም ውድ አንባቢዎቼ የዚህን ተቋም ፍላጎት ሳትገነዘቡት የምትቀሩ አይመስለኝም፡፡ በስም 'የጋዜጠኞች መብት አስከባሪ' የሆነው ሲ.ፒ.ጄ፤ ላዩ ላይ ከለጠፈው ስያሜ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ የእንግሊዝ መንግስት 'ንጉሳዊያን ቤተሰቦችን ተዳፍሯል' በሚል እሳቤ የተዋጣለት ሙያዊ (Professional) ስራዎችን የሚያከናውነውን አልጀዚራ ቴሌቪዥንን ሲያግድ ትንፍሽ ሊል አልፈቀደም፡፡

ይህ ብቻ እንዳይመስላችሁ፡፡ የአሜሪካ የጦር ኃይል ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ እና በኢራቅ ቆይታው ለዜና ፍጆታ የሚሰራጩ ዘገባዎችን በይፋ ሲገድብ፣ ሆን ብሎ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞችን ለመግደል ኢራቅ የሚገኘውን የአልጀዚራን ቴሌቪዥን መቀመጫው ከሆነው ሆቴሉ ጋር ሲያጋይ እንዲሁም የውጭ ጋዜጠኞችን በሚታወቁ አካባቢዎች ለረጅም ጊዜ በእስር ላይ ማቆየቱን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ይፋዊ

መግለጫ  አላወጣም፡፡ ሀገሪቱ በዚህ ሁኔታ የፕሬስ ነጻነትን እየጣሰች መሆኗን እያወቀ፣ የማባባል ዓይነት የውስጥ ማስታወሻ ከመጻፍ በስተቀር አንዳችም ያለው ነገር የለም፡፡ኧረ ለመሆኑ ለሲ.ፒ.ጄ የአልጀዚራ ቴሌቪዥን ተግባር የሚዲያ ስራ አይደለምን?፣ በአሜሪካ ጦር ኃይል የሚገደሉትና ያለምንም የፍርድ ሂደት  የሚታሰሩበት ጋዜጠኞች አይደሉምን?...

እነዚህ ጥቂት ተጨባጭ  ሃቆች የሚያመላክቱት፤ የሲ.ፒ.ጄ  ጉዳይ ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር  የተያያዘ ሳይሆን፤ ፍላጎቱ  ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓላማዊ መሆኑን ነው፡፡ ለም ቢባል፤ ከተቋሙ ጋር  ተመሳሳይ  ርዕዮተ - ዓለም  የሚያራምዱ ሀገሮች ፕሬስን ሲረግጡና ጋዜጠኞችን  ሲገድሉ ብሎም ያለፍርድ  ሲያስሩ ዝምታን እየመረጠ፣ ሀገራችን የህግ አግባብን ተከትላ በወሰነችው ውሳኔ ላይ ለመጮህ መፈለግ በምንም ዓይነት  ስሌት “ የጋዜጠኞች  ተቆርቋሪ” ሊያስብል የሚያስችል  ባለመሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው የአሜሪካን ምስጢራዊ  ሰነዶችን ሳይቀር ቦርቡሮ በማውጣት  የሚታወቀው  “ዊክሊክስ” የተሰኘው ድረ - ገጽ፤ በቅርቡ ሲ.ፒ.ጄን ‘የእናንተ ስራ ለጋዜጠኞች መቆርቆር አለመሆኑን እናውቃለን’ በማለት እውነተኛ ስራው ሌላ  መሆኑን ያጋለጠው፡፡

ይህን ዓለም ያወቀውን የሲ.ፒ.ጄን ተግባር እዚህ ላይ ልተወውና የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ወደ አወጣውና ከበርካታ ወቀሳዎች ጋር “ከአንድ ወንዝ የተቀዳ”  ወደሚመስለው  መግለጫ ልውሰዳችሁ፡፡  የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ “...በኢትዮጵያ ያለውን የፍርድ አሰጣጥ  ሂደት፣ የሀገሪቱ  መንግስት በሽበርተኝነት ላይ ያለውን  ህጋዊ ስጋት  እንዲሁም ሀገሪቷ ብሔራዊ  ደህንነቷን ለመጠበቅ  ላላት ፍላጎት ዕውቅና ይሰጣል፤ ይሁንና ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር እያካሄድን ባለነው  የሰብዓዊ መብቶች ውይይቶች  ላይ ግልጽ እንዳደረግነው፣ ለዴሞክራሲያዊ ማህብረሰብ ነጻ ፕሬስ አስፈላጊ ነው” በማለት  የሽብርተኝነት  ወንጀል  ስጋትን ሀገራቸው ያለ ፍርድ  ሂደት ስትከላከለወ ‘ትክክል’፣ ሌላው  ሀገር ደግሞ በህግ  አግባብ ብሔራዊ ጸጥታውን ሲያስከብር ‘ የተሳሳተ ነው’ ለማለት ሞክሯል፡፡

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ይህ የዋሽንግተን መግለጫ “እኛ ብቻ ነን እንጂ፤ ሌላ ሀገር  በህጋዊ መንገድም ቢሆን ምንም ማድረግ  አይችልም”  የሚል አንድምታ ያለው ነው፡፡ ተደጋግሞ በሚዲያዎች እንደሚለገለጸው፤ ከመስከረም አስራ አንዱ የሽብር ጥቃት ጋር  በተያያዘ የአሜሪካ  ጦር ኃይል በኩባዋ “ጓንታናሙ ቤይ” ውስጥ ድብቅ

እስር ቤትን መስርቶ ተጠርጣሪዎችን ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ውጭ አስከፊ ተግባር ሲፈጽምባቸው እንደነበር የአደባባይ ምስጢር ነው – የሲ.ፒ.ጄ የውስጥ ማስታወሻ ላይስሙላም ቢሆን እንደሚገልጸው። አሜሪካ ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ የሚዲያ ውጤቶችን አግዳለች፣ ጋዜጠኞችን ገድላለች፣ ያለ ፍርድ አስራለች፡፡ ነገሩ ለአንባቢዎቼ ግልጽ ይሆን ዘንድ ከእነዚህ ጥሰቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ልግለጽላችሁ፡፡...

አንዷት በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ 'በፓሽቶ ቋንቋ" አገልግሎት ውስጥ የምትሰራ ጋዜጠኛ፤ የአፍጋኒስታን ታሊባን መሪ ሙላህ ሞሐመድ ኡመርን ስላናገረች ከሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተደረሰባት ተፅዕኖ ስራዋን ለመልቀቅ ተገድዳለች፡፡ እ.ኤ.አ በህዳር 2001 በአሜሪካ መራሹ የአፍጋኒስታን ዘመቻ፤ የአሜሪካ ጦር ካቡል የሚገኘውን የአልጀዚራ ጣቢያ ቢሮን መትቷል - ምንም እንኳን ቢሮው ላይ በርካታ የማሰራጫ ሳተላይቶች ተንጠልጥለው በግልጽ ቢመለከትም፡፡ ሁኔታውንም አንድ ታዋቂ የአሜሪካ ጋዜጠኛና ደራሲ እ.ኤ.አ በሰኔ 2006 እንደተናገረው፤ ጥቃቱ "ለአልጀዚራ ጣቢያ ግልጽ መልዕክት ለማስተላለፍ ሆን ተብሎ የተፈጸመ ነው" ብሏል፡፡

ታዲያ በሀገራችን ፍርድ ቤት ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ የተዳኙትን ወንጀለኞች አስመልክቶ "...ለዴሞክራሲያዊ ማህብረሰብ ነጻ ፕሬስ አስፈላጊ ነው፡፡..." በማለት መግለጫ ያወጣው የአሜሪካ መንግስት ያለ ተጨባጭ ማስረጃና ያለ ፍርድ የተካሄዱ የፕሬስ አፈናዎች በዚህ ብቻ የሚያበቁ እንዳይመስላችሁ፡፡ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 8 ቀን 2003 ማለዳ ላይ በአሜሪካ መራሹ የኢራቅ ዘመቻ፣ የዋሽንግተን ጦር ባግዳድ የሚገኙትን የአልጀዚራ ጣቢያን ቢሮን፣ በአቅራቢያዊ የሚገኘውን የአቡዳቢ ቴሌቪዥንን እንዲሁም የዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች ማረፊያ ማዕከል የሆነውን የፍልስጤሞች ሆቴልን በታንክ አረር አውድሟል፡፡ በዕለቱ ጥቃትም ሁለት ጋዜጠኞች ሲሞቱ፣ ሶስቱ ቆስለዋል፡፡

ስለ ነጻ ፕሬስ አስፈላጊነት በመግለጫው ያተተው የዋሽንግተን አስተዳደር፣ ጋዜጠኞችን ያለምንም ተጨባጭ ማስረጃና የፍርድ ሂደት ለረጅም ጊዜ በእስር ላይ ያቆያል የሚል ክስም ቀርቦበታል፡፡ በኢራቅ ዘመቻ ወቅት የአሜሪካ ኃይሎች የአካባቢውን ፎቶ ግራፈሮችና የካሜራ ባለሙያዎችን ማስረጃ ሳይኖራቸው ከማሰራቸውም በላይ፤ ለ"CBS" የዜና አውታር፣ ለሮይተርስ፣ ለአሶሾየት ፕሬስ እና ለአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የሚሰሩና ሌሎች ጋዜጠኞችን ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለረጅም ጊዜ በጥርጣሬ በእስር ላይ እንዲቆዩ አድርገዋል፡፡

እርግጥ ይህን የአሜሪካን ተግባር የተመለተ እንደ እኔ ያለ ሰው፤ ‘አሜሪካ ራሷ እንዳሻት የምትጨፈልቀውን የፕሬስ ነጻነት ነው እንዴ፣ በሌሎች ሀገራት በመግለጫ መልክ ትምህርታዊ ማብራሪያ የምትሰጠው?!’ በማለት መደመሙ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ አዎ! ነገሩ የሚያስገርም ነው፡፡ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት አሸባሪነትን ከአጋሮቹ ጋር ሆኖ እየተዋጋ ነው፡፡ ይሁንና በአሸባሪነት የሚጠረጥራቸውን ሰዎች፤ ጋዜጠኛ ሆኑ አልሆኑ አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ጉዳያቸው ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል እንጂ፤ ከጥርጣሬ ተነስቶ በወታደሮቹ አይገድልም፤ ሰብዓዊ መብታቸውንም አይገፍም፡፡ የሁለቱ ስዊድናዊያን አያያዝና የሰሞኑ ፍትሐዊ ቅጣትም የዚህ ማንነቱ መገለጫ ይመስለኛል፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፤ የአሜሪካ መንግስት መግለጫ በአንድ ወቅት በአይጋ ፎረም ድረ - ገጽ ላይ “በሽብተኝነት ላይ የምዕራቡ ዓለም መንታ ገጽታ” /Western double face on terrorism/ በሚል በአንድ ኢትዮጵያዊ የቀረበን ዓይነ - ግቡ ጽሑፍ አስታውሶኛል፡፡ እንደ ጸሐፊው ምልከታ፤ በኢትዮጵያም ሆነ በምዕራቡ ዓለም በአሸባሪነት የተፈረጁ ቡድኖች በእኩል ዓይን መታየት አለባቸው፡፡ ምዕራባዊያን ከኢትዮጵያ ጋር አሸባሪነትን በጋራ እየተዋጉ ቢሆንም በግብረ - ሽበራው ስራ ላይ የሚሳተፉ ቡድኖች በእኩልነት አይታዩም ያሉት ጸሐፊው፤ ይህም የምዕራቡ ሀገራት ስለ ሽብርተኝነት ያላቸውን “መንታ ገጽታ” የሚያመላክት መሆኑን አስረግጠው አብራርተዋል፡፡

እርግጥም የዋሽንግተኑ አስተዳደር በመግለጫው በአንድ በኩል “...የኢትዮጵያ መንግስት በሽብርተኝነት ላይ ያለውን ህጋዊ ስጋት ዕውቅና እንሰጣለን...” እያለ በሌላ በኩል ደግሞ”...ለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ፕሬስ አስፈላጊ ነው...” የሚሉ እርስ በርሳቸው የማይገናኙ አባባሎችን መጠቀሙ “የመንታ ገጽታ” አካሄዱ ሁነኛ አስረጅ ይመስለኛል፡፡

አንድን የግብረ - ሽበራ ተግባር ለመቆጣጠርና በእንጭጩ ለመቅጨት የሚደረግ ህጋዊ ጥረትን የሚደግፍ አካል፤ በየትኛውም አመክንዮ ጥረቱን ግንኙነት ከሌለው የሚዲያ አሰራር ጋር በግድ አጣብቆ ሊሰፋው መሞከር የለበትም– አሸባሪዎችንና ግብረ አበሮቻቸውን ይኮንናል እንጂ፡፡ በመሆኑም የኋይት ሃውሱ መግለጫ እውነታውን እያወቀ ለነጮች በማበር የቀረበ እንጂ፤ በምንም ዓይነት መስፈርት ሃቁን ያገናዘበ ነው ሊባል የሚችል አይመስለኝም፡፡

ደጋግሜ እንደገለጸኩት፣ የሁለቱ ስዊድናዊያን የፍርድ ሂደት ከሚያከናውኑት የሚዲያ ስራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡ ጋዜጠኛ በመሆናቸው የተወሰነባቸው ምንም ዓይነት ቅጣት የለም፡፡ የተያዙትና የቅጣት ውሳኔው የተላለፈባቸው የሀገራችንን ሉዓላዊ የፖለቲካ ነጻነት በመጋፋት በአሸባሪዎች እየታገዙ በህገ - ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው ነው፡፡ የአሜሪካ መንግስት ግን ይህን እውነታ ወደ ጎን ብሎ፣ ጉዳዩን በግድ ከጋዜጠኝነት ስራ ጋር ለማቆራኘት መሞከሩ ከቶ ምን ይሉት አስተያየት በፍፁም ሊገባኝ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡

ሀገራችን እነዚህን ሰዎች በጋዜጠኝነት ተግባራቸው ሳይሆን፣ በህገ -ወጥ ድርጊት የተሰማሩትን ስዊድናዊያን በአጭር ጊዜ ፍትህ እንዲያገኙ ማድረጓ፣ በድብቅ እስር ቤቶች ሳይሆን፣ ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ ቤተሰቦቻቸው እንዲጎበኛቸው መፍቀዷ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ህግጋትን ተከትላ የፍርድ ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረጓ ይሆን እንዴ– ዋሽንግተኖችን እንዲህ ያበሳጫቸው?... እርግጥም ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውና በአፍጋኒስታንና በኢራቅ በውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ላይ ካካሄዷቸው ሙያዊና ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አንጻር፣ አሜሪካ "በህግ የተደገፈም ቢሆን፣ ማንኛውም ነገር እኔ ሳደርገው እንጂ፣ ሌላው ወገን ሲከውነው ተቀባይነት የለውም" የሚል የውስጥ ህግ ያወጣች ያስመስልባታል፡፡

ይሁንና ሀገራት በእንዲህ ዓይነቱ የህግ የበላይነት ማስከበር ስራዎች ተግተው ሲሰሩ ማበረታታት የሚጠበቅባት ይህች ሀገር፣ "እኔ ህገ - ወጥ ተግባር ብፈጽምም ትክክል ነኝ፣ እናንተ ግን ህግን ተመርኩዛችሁም ቢሆን የምታከናውኑት ድርጊት እገሌ ከሚባል ሙያ ጋር የሚገናኝ ስለሆነ አግባብ የለውም" ማለቷ ተገቢነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊም አስተሳሰብ ጭምር ይመስለኛል፡፡

በጥቅሉ በሁለቱ ስዊድናዊያን ላይ የተላለፈው ቅጣት "ጫጫታ" መንስዔዎች "ነጮች እንዴት በጥቁሮች ይዳኛሉ?!" የሚልና ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋር የማይሄድ አመለካከት እንዲሁም "እኛ ብቻ ነን ትክክል" በሚል ክንዋኔውን ከሰብዓዊ መብትና ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር በኃይል ለማገናኘት መጣር ናቸው፡፡

ሆኖም እንዲህ ዓይነቶቹ አስተሳሰቦች፣ የአንድን ሀገር የፍትህ ሥርዓት ተጻርሮ በመቆም፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊ ነጻነት የመገፋት፣ ምናልባትም በሰሞታ አቅራቢዎቹና

በሌላው ሀገር መካከል ሊኖር የሚችለውን የፈካና ዘመናትን ያስቆጠረ ግንኙነት የሚያቆረፍድ እንጂ፤ ሌላ ረብ ያለው ጥቅም የሚያስገኝ አይመስለኝም፡፡ በመግለጫ ስም የሚካሄዱ ፍትህን የመቀልበስ አካሄዶችን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይቀበላል ብሎ ማሰብም፤ ስለ ሀገሪቱ ታሪካዊ ሁኔታ በውል ካለማወቅ የመነጨ ሊሆን ስለሚችል እውነታውን ዞር ብሎ መመልከት ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡